## ርዕስ፦ ከባዶነት ወደ ሙላት – የሚታደገው አምላክ (ሩት 1–4)

**መግቢያ** የሩት መጽሐፍ ትንሽ ታሪክ ቢሆንም ትልቅ መልዕክት ያለው ነው። ይህ ታሪክ የ ሁለት መበለቶች፣ የአንዲት መጻተኛ፣ የአንድ ጻድቅ ሰው እና የማዳን እጁ የማይታይ የታዳ ጊው አምላክ ታሪክ ነው። በረሃብ፣ በሞት እና በጥልቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ፣ እግዚአብሔ ር ዛሬም ድረስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ወደ እኛ ሕይወት የሚያመለክተውን የቤዛነት ታ ሪክ በዝግታ ይህ መጻሐፍ ይዘግባል።ከዚህ እውነት አንጻር በዛሬው መልዕክት **እግዚአብሔር በባዶነታችን ውስጥ ይገናኘናል፤ በታማኝ ፍቅሩ፣ ዋጋ በ ሚያስከፍል ኃላፊነት እና በጸጋው አካታችነት ይቤዠናል** የሚለውን የመንግስቱን እውነት እንመልከታለን።ለዚህም በሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ እናተኩራለን **የባዶነት ሕመም** **የታ ማኝ ፍቅር መንገድ** **የቤዛነት ኃይል**

## I. የባዶነት ሕመም (ሩት 1)

የሩት መጽሐፍ የሚጀምረው በሐዘን ነው። ረሃብ አቢሜሌክንና ኑሀሚንን ከቤተልሔም ወደ ሞዓብ እንዲሰደዱ ያደርጋቸዋል። በዚያም ኑሀሚን ባሏንና ሁለቱን ልጆቿን ታጣለች።በዚህ ምክንያት "በሙላት ወጣሁ እግዚአብሔርም ወደ ቤቴ ባዶዬን መለሰኝ እግዚአብሔር አዋርዶኛልና ሁሉን የሚችል አምላክ አስጨንቆኛል" በማለት ወደ ቤቷ ትመለሳለች።

- **ባዶነት ለእግዚአብሔር ሕዝቦችም ቢሆን እውነተኛ ስሜት ነው፦** ኑሀሚን አማኝ ናት፤ ነገር ግን ተመርራለች፣ ቆስላለች፣ ግራ ተጋብታለች። እግዚአብሔር በእሷ ላይ እንደተነሳ ባት ይሰማታል።
- **ዛሬም በቤተክርስቲያን ብዙዎች እንደ ኖሀሚን ይሰማቸዋል፦** በሞት፣ በፈረሰ ግንኙነት ፣ በገንዘብ ችግር፣ በመንፈሳዊ ድርቀት ወይም በውድቀት ምክንያት ባዶነት ይሰማቸዋል ።
- **ተጥለናል ብለን ስናስብ እንኳ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፦** ኑሀሚን ሕይወቷን **"እግ ዚአብሔር አሳዘነኝ"** ብላ ብትተረጉመውም፣ እግዚአብሔር ግን በዚያው ወቅት ሥራው ን እየሠራ ነበር፦ "እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደጎበኘና ምግብ እንደሰጣቸው" ሰማች፤ ሩትም ከጎኗ ቆማለች።

**ተግባራዊ ትምህርት፦** እንደ ኑሀሚን **"ተመርሬአለሁ፣ ባዶነት ይሰማኛል"** ብሎ ማመን መንፈ ሳዊ አለመሆን አይደለም። እግዚአብሔር የልጆቹን ቅን የሐዘን ድምፅ መስማት ይችላል። ባዶነ ት የታሪኩ ማብቂያ አይደለም። የወደፊት ተስፋ የለም ብለን በምናስብበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለኛ የማይታየንን የቤዛነት ዘር እያበቀለ ሊሆን ይችላል።ስለዚህ እንመነው።

## II. የታማኝ ፍቅር መንገድ (ሩት 1–2)

**የሩት የቃል ኪዳን ፍቅር፡-** በኑኅሚን መራራነት መካከል፣ ሩት በሚያስደንቅ **የቃል ኪዳን ፍቅር ታበራለች** ሞዓባዊቷ ሩት የኑሀሚንን አምላክና ሕዝብ ትመርጣለች "አንቺ ወደምትሄጂበት እሄዳለሁ… ሕዝብሽ ሕዝቤ፣ አምላክሽም አምላኬ ይሆናል።" ይህን በመናገሯ ሩት ራሷን ከኑኃሚን ጋር ብቻ ሳይሆን ከእስራኤል አምላክ ጋር አቆራኝታለች።

**የሩት ትሕትና እና ታታሪነት፡-** ድሆች በሚሠሩበት መስከ ቃርሚያ ለመቃረም ትወጣለች፤ ***ሩት 2:3 "ሄደችም፥ ከአጫጆች በኋላ በእርሻ ውስጥ ቃረመች እንደ ኢጋጣሚም ወደ የአቤሜሌክ ወገን ወደ ነበረው ወደ ቦዔዝ እርሻ ደርስች።"*** ምንባቡ **"እንደ ኢጋጣሚ"** ይላል። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ነገረ መልኮት ውስጥ "**ኢጋጣሚ"** የሚባል ነገር የለም። ለእኛ በኢጋጣሚ የሆነ የሚመስለው ነገ ር እውነቱ መለኮታዊ ጥበቃን የያዘ መሆኑ ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ክስተቶችን እንደ ፈቃዱ የሚያስተዳድር ስልሆነ ።

**የእግዚአብሔር መንግሥት ብዙውን ጊዜ አይታይም እንጂ መቼም ቢሆን ሥራ አያቆምም ስለዚህ፡-** በማይታወቁ የሕይወት ወቅቶቻችን ውስጥ፣ እግዚአብሔር አሁንም እየመራን ነ ው። በተለመደው የዕለት ተዕለት ተግባር ውስጥ፣ እግዚአብሔር አሁንም እየሠራ ነው በዝ ምታ ጊዜያት ውስጥ፣ እግዚአብሔር አሁንም አብሮን አለ።

**የቦዔዝ ቸርነት**፡-የእግዚአብሔር መንግስት ሥነ-ምግባር በተግባር ቦዔዝ ሕጉን ከመፈጸም ባለፈ ለሩት ጥበቃ ያደርጋል፣ በደግነት ያናግራታል፣ በልግስናም ያቀርብላታል።ቦኤዝ የሚያየው አንዲት ድሃ መጻተኛን ብቻ ሳይሆን፣ ክብር ያላት ን ሴት ነው፤ በክብርም ያስተናግዳታል፣የእግዚአብሔር መንግሥት **ፍቅርና ታማኝነት** እንጂ አ መቺ ሁኔታን ተከታይነት አይደለምና። ነገሮች መራራ ሲሆኑም ከቤተሰብ፣ ከቤተክርስቲያንና ከጓደኞች ጋር መቆምን ይጠይቃል።

## III. የቤዛነት ኃይል (ሩት 3–4)

የታሪኩ ትልቅ ለውጥ "የቅርብ ዘመድ ተቤዢ" (Go'el) የሚለው ሐሳብ መከሰቱ ነው። ይህ ዘመድ መሬትን የመመለስ፣ ለሟቹ ስም የማ ስቀጠልና ቤተሰብን የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት ሰው ነው።በዚህ መሰረት ተቤዢው ቦዔዝ ሥልጣኑን ሌሎችን ለመበዝበዝ ሳይሆን ለመጠበቅ፣ ጥቅምን ለ ማሳደድ ሳይሆን የታሪክን ስም ለመመለስ ተጠቀመበት።**የቤዛነቱ ፍሬ ከመራራነት ወደ በረ**

**ከት፡-** በአንድ ወቅት “ማራ (መራራ) በሉኝ” ያለችው ኑህሚን፣ አሁን ሕፃኑን ኢዮቤድን በ ታቀፈች ጊዜ ባዶነቷ ወደ ሙላት ተለወጠ።

**ከኢዮቤድ እስከ ክርስቶስ ያለው ትልቁ ታሪክ፡-** ፡- መጽሐፉ የሚደመደመው በዘር ሐረግ ነው   ይህም ኢዮቤድ፣ እሴይ፣ ዳዊት በሚል።በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደምልመለከትው እግዚአብሔር የአንድን ቤተሰብ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የመንግሥቱን ዕቅ ድ እያስቀጠለ ነበር። በሞዓባዊቷ ሩት በኩል እግዚአብሔር የታላቁን ንጉሥ የዳዊትን እና በ መጨረሻም የዳዊት ልጅ የሆነውን የኢየሱስን የዘር ሐርግ መስመር እያዘጋጀ ነበር።

**የወንጌል ተግባራዊ ትምህርት፡-** ቦዔዝ የኢየሱስ ምሳሌ ነው። ቦዔዝ የቤተሰቡ ዘመድ ነበር ፤ ኢየሱስም የእኛ “ዘመድ” (ቤዛ) ለመሆን ሰው ሆነ። ቦዔዝ ዋጋውን ለመክፈል ፈቃደኛ ነበር፤ ኢየሱስም የቤዛነታችን ን ዋጋ በገዛ ደሙ ከፈለ። ቦዔዝ መጻተኛዋን ወደ እስራኤል የቃል ኪዳን ቤተሰብ አስገባት፤ ኢየሱስም ኃጢአተኞችንና ከየአሕዛቡ የሆኑትን ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ አመጣ።

**ማጠቃለያ**፡-የሩት መጽሐፍ በረሃብ፣ በሞትና በመራራነት ይጀምራል፤ ነገር ግን በሕፃን ልጅ፣ በታደሰ ቤተሰብና በንጉሣዊ የዘር ሐረግ ይጠናቀቃል። እግዚአብሔር እንዲህ ነው፤ ወደ ተሰበ ሩ ታሪኮች ውስጥ ገብቶ የቤዛነትን ታሪክ ይጽፋል። ስለዚህ ባዶነታችሁን ወደ ተቤዢው ጌታ አምጡ። እንደ ሩት ታማኝነታችሁንና ፍቅራችሁን ስጡ። እንደ ቦዔዝ ጥንካሬአችሁንና ሀብታ ችሁን ለበጎ ተጠቀሙበት። የኑህሚን ዕንባ ወደ ደስታ፣ የሩትንም ውርደት ወደ ክብር የለወጠ አምላክ ዛሬም በዝግታና በታማኝነት በእናንተ ውስጥ መንግሥቱን እየገነባ እንደሆነ እመኑ።**አ ሜን**